# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የትምህርት ቢሮ

## Central Ethiopia Region Government

## Bureau Of Education


ቀን/Date: ህዳር 16 ቀን 2017

ቁጥር/Ref.No: 105/ለ30-886/ለ7/35

ለ_____________________ዞን ትምህርት መምሪያ

ለ_____________________ልዩ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት

ባሉበት

**ጉዳዩ፡- መመሪያ ስለመላክ፤**

ትምህርት ቤቶች በሠለጠኑና የተሻለ የሙያ ብቃት ባላቸው የሰው ሀይል እንዲመሩና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን የትምህርት ቤት አመራር ሪፎርም ለማድረግ የምልመላ፣ መረጣ እና ምደባ የአፈፃጸም ስርዓት መመሪያ ቁጥር 01/2016" ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መሆኑን ተከትሎ 72 በመቶ በላይ የትምህርት ቤት አመራር የስራ መደቦች ላይ ምደባ መፈጸሙ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም በቀሪዎቹ 28 በመቶ በሚጠጉ ክፍት የትምህርት ቤት አመራር የስራ መደቦችና በሂደትም በተለያዩ ምክንያቶች በሚለቀቁ የትምህርት ቤት አመራር የስራ መደቦች ላይ ጊዜያዊ የትምህርት ቤት አመራር ስምሪት ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

ስለሆነም የተዘጋጀውን መመሪያ 19 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የተላከ ሲሆን ከህዳር 16 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ በጥንቃቄ ተፈፃሚ እንዲሆን እየገለጽኩ፤ በመመሪያው በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለአንድ ጊዜ ብቻ የትምህርት ቤት አመራር ጊዜያዊ ስምሪት በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ደረጃ እንዲካሄድ ውክልና የተሰጠ በመሆኑ በተቀመጠው አግባብ ተግባራዊ እንዲደረግ አሳስባለሁ፡፡

//ከበጎ ምኞት ጋር//

አንተነህ ፈቃዱ ወ/ሰንበት
የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስ[ት]
ም/ርዕሰ መስተዳድር ፤ የማህበራ[ዊ]
ክላስተር አስተባባሪ እና የትምህርት
ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ፤

*በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል*

- ለርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
- ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ
- ለመምህራን ማህበር ጽ/ቤት

  ባሉበት
- ለ_____________________ዞን/ልዩ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት

  ባሉበት
- ለቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት
- ለ_____________________ዘርፍ
- ለመምህራንና ሠራተኞች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

  ትምህርት ቢሮ

# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል
# ትምህርት ቢሮ

## የትምህርት ቤት አመራሮች ጊዜያዊ የስምሪት
## አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 06/2017

ህዳር/2017 ዓ/ም

ትምህርት ቢሮ

## መግቢያ

ትምህርት ቤቶች ብቁ ዜጎች የማፍራት ተልዕኮአቸውን እውን እንዲያደርጉ፣ የመምህሩ ስራ ይበልጥ ፍሬያማ ሆኖ የመማር ማስተማሩ ስራ ውጤታማ እንዲሆን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ የሚጠይቅ ቢሆንም የትምህርት ቤት አመራሮች ሚና የጎላ ነው፡፡

በክልሉ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በሠለጠኑና የተሻለ የሙያ ብቃት ባላቸው የሰው ሀይል እንዲመሩና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን የትምህርት ቤት አመራር ሪፎርም ለማድረግ የምልመላ፣ መረጣ እና ምደባ የአፈፃጸም ስርዓት መመሪያ ቁጥር 01/2016 ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት በየደረጃው በሚፈጠሩ ክፍት የትምህርት ቤት አመራር የስራ መደቦች ተለይተው በየዓመቱ ወይም በየሴሚስተር መጨረሻ የመማር ማስተማር ሂደትን በማይጎዳ መልኩ ክልላዊ የትምህርት ቤት አመራር ውድድር በማካሄድ በቋሚነት ምደባ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

በመሆኑም የትምህርት ቤት አመራር ውድድር ተካሂዶ በቋሚነት እስኪመደቡ ድረስ ክፍት በሚሆኑ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች በሚለቀቁ የሱፐርቫይዘር ወይም የርዕሠ-መምህር ወይም የምክትል ርዕሠ-መምህር የስራ መደቦች ላይ ጊዜያዊ የትምህርት ቤት አመራር ስምሪት ለመስጠት የሚያስችል ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ስለሆነም ቢሮው በተሻሻለው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 199/2015 ዓ/ም አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 11 በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት ይህን የትምህርት ቤት አመራሮች ጊዜያዊ የስምሪት አፈፃጸም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ትምህርት ቢሮ ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች ጊዜያዊ የስምሪት አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 06/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡

(1) "ክልል" ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ነው፤

(2) "ቢሮ" ማለት የክልሉ ትምህርት ቢሮ ነው፤

(3) "ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር" ማለት ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር፣ ተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህር እና ተጠባባቂ ሱፐርቫይዘር ለማለት ነው፡፡

(4) "ተጠባባቂ ርዕሰ-መምህር" ማለት በትምህርት ቤቱ አጠቃላይ የትምህርት ሂደቱን በበላይነት የሚመራ ርዕሰ መምህር ባልተመደበበት ወይም ተመድቦ በተለያዩ ምክንያቶች በሚለቅበት ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር በውድድር እስኪመደብ ድረስ ተክቶ የሚሰራ መምህር ነው፡፡

(5) "ተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህር" ማለት የትምህርት ሂደቱን በምክትል ኃላፊነት የሚመራ ምክትል ርዕሳነ መምህራን ባልተመደቡባቸው ወይም ተመድበው በተለያዩ ምክንያቶች በሚለቁበት ትምህርት ቤቶች ምክትል ርዕሰ መምህራን በውድድር እስኪመደቡ ድረስ ተክቶ የሚሰራ መምህር ነው፡፡

(6) "ተጠባባቂ ሱፐርቫይዘር" ማለት ለትምህርት ቤቶች በዋናነት በመማር ማስተማር ሂደት እንዲሁም በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የአቅም ግንባታ፣ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግ ሱፐርቫይዘር ባልተመደበበት ወይም ተመድቦ

በተለያዩ ምክንያቶች በሚለቁበት የሱፐርቫይዘር የስራ መደብ ሱፐርቫይዘሮች በውድድር እስኪመደቡ ድረስ ተክቶ የሚሰራ ባለሙያ ወይም ቡድን መሪ ነው፡፡

(7) "ጊዜያዊ የስምሪት መመሪያ" ማለት የትምህርት ቤት አመራሮች ምልመላ፣ መረጣ እና ምደባ የአፈፃጸም ስርዓት መመሪያ ቁጥር 01/2016" ተግባራዊ ሲደረግ ክፍት በሚሆኑና በተለያዩ ምክንያቶች በሚለቀቁ የርዕሠ-መምህር፣ የምክትል ርዕሠ-መምህርና የሱፐርቫይዘር የስራ መደቦች ላይ በጊዜያዊነት ለተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር ስምሪት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ነው፡፡

(8) "የተጠባባቂ አበል" ማለት ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች በትምህርት ዝግጅታቸውና በሚመደቡበት የትምህርት እርከን ታሳቢ በማድረግ ቀደም ሲል ከሚያገኙት ደመወዝ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ መሰረት የሚከፈላቸው ጥቅማ-ጥቅም ሲሆን ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር በመምህርነት ወይም በባለሙያነት ወይም በቡድን መሪነት ይከፈለው የነበረው ደመወዝ ከሚመደብበት የትምህርት ቤት አመራር ለስራ መደብ የተፈቀደውን መነሻ ደመወዝ የደረሰ ወይም ያለፈ ከሆነ የተጠባባቂ አበል አይመለከተውም፡፡

(9) "በወንድ ፆታ" የተገለጸው አገላለጽ ሴቶችንም ያጠቃልላል፡፡

3. <u>ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች</u>

(1) ዋና ዓላማ

ክፍት በሚሆኑ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች በሚለቀቁ የሱፐርቫይዘር ወይም የርዕሠ-መምህር ወይም የምክትል ርዕሠ-መምህር የስራ መደቦች ላይ የትምህርት ቤት አመራሮች በውድድር በቋሚነት እንዲመደቡ እስኪደረግ ድረስ ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር በማሰማራትና የተጠባባቂ አበል በመክፈል ለሚሰሩት ስራ ሙሉ ኃላፊነትና ተጠያቂነትን በመስጠት የመማር ማስተማሩ ስራ በውጤታማነት እንዲከናወን ለማድረግ ነው፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

(2) ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ) የትምህርት ቤት አመራር በቋሚነት ባልተመደቡባቸው ወይም ተመድበው በተለያዩ ምክንያቶች በተለቀቁ የስራ መደቦች ላይ ባጠረ ጊዜ ውስጥ ስምሪት በመስጠት የመማር ማስተማሩን ስራ ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ

ለ) ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች በመምህር ወይም በባለሙያ ወይም በቡድን መሪ የስራ ደረጃ ከሚያገኙት ደመወዝ በተጨማሪ የማበረታቻ አሰራርን በመዘርጋት ሙያውን ተመራጭ ለማድረግ ፣

ሐ) በትምህርት ቤቶች ከሚገኙ መምህራን መካከል የተሻለ አፈፃጸም ያላቸውን መምህራን በመለየት በጊዜያዊነት ስምሪት በመስጠት እንዲበረታቱ ለማድረግ፣

መ) የሰለጠኑ፣ ብቃት፣ ተነሳሽነትና መልካም ስነ-ምግባር ኖሮአቸው የስራ ልምድ ባለማሟላታቸው ምክንያት ወደ ትምህርት ቤት አመራርነት መምጣት ያልቻሉትን መምህራንን ወደ አመራርነት በመሳብ የሚሰጣቸውን ተግባር በበለጠ ውጤታማነት እንዲያከናውኑ ለማበረታታት ነው፡፡

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

የትምህርት ቤት አመራሮች ምልመላ፣ መረጣ እና ምደባ የአፈፃጸም ስርዓት መመሪያ ቁጥር 01/2016" ተግባራዊ በማድረግ ለትምህርት ቤት አመራሮች በቋሚነት ምደባ እስኪፈጸም ድረስ በተጠባባቂነት በተመደቡ ርዕሠ-መምህራን፣ ምክትል ርዕሠ-መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ Central Ethiopia Regional State Education Bureau

## ክፍል ሁለት

## ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር ስምሪት አፈፃጸም

5. <u>የትምህርት ቤት አመራሮችን በተጠባባቂነት ማሰራት ስለሚቻልበት ሁኔታ</u>

(1) በትምህርት ቤት ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር ወይም ምክትል ርዕሠ-መምህር የሚመደበው ርዕሠ-መምህር ወይም ምክትል ርዕሠ-መምህር በውድድር በቋሚነት ባልተመደበበት ወይም በውድድር በቋሚነት የተመደበው ርዕሠ-መምህር ወይም ምክትል ርዕሠ-መምህር በተለያዩ ምክንያቶች በለቀቀባቸው ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

(2) በልዩ ወረዳ ወይም በወረዳ ወይም በከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ተጠባባቂ ሱፐርቫይዘር ወይም ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር የሚመደበው በውድድር በቋሚነት ባልተመደበበት ወይም በውድድር በቋሚነት የተመደበው ሱፐርቫይዘር ወይም ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር በተለያዩ ምክንያቶች በለቀቀባቸው የስራ መደቦች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

6. <u>የተጠባባቂ ትምህርት ቤት አመራሮች ስምሪት አፈፃጸም</u>

(1) ክፍት ለሆነው የርዕሠ-መምህር ወይም የምክትል ርዕሠ-መምህር የስራ መደብ ላይ ከትምህርት ቤቱ መምህራን መካከል በውድድር በመምረጥ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር ወይም ምክትል ርዕሠ-መምህር መድቦ ማሰራት ይቻላል፡፡

(2) ክፍት ለሆነው የከፍተኛ ሱፐርቫይዘር ወይም የሱፐርቫይዘር የስራ መደብ ላይ ከልዩ ወረዳ ወይም ከወረዳ ወይም ከከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት የዓላማ ፈፃሚ ዳይሬክቶሬት ቡድን መሪዎች ወይም ባለሙያዎች መካከል በውድድር በመምረጥ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ተጠባባቂ ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር ወይም ተጠባባቂ ሱፐርቫይዘር በመምረጥ መድቦ ማሰራት ይቻላል፡፡

(3) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር የተያዙ የስራ መደቦች በትምህርት ቤት አመራር ምልመላ፣ መረጣና ምደባ አፈፃጸም መመሪያ መሰረት



በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

በማድረግ በውድድር ቋሚ ምደባ በአንድ ዓመት ጊዜ ካልተፈጸመ ምደባ እስኪፈጸም ድረስ ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሩን የግብ ስምምነት አፈፃጸም ውጤት ደረጃ ሁለትና በላይ የአፈፃጸም ደረጃ መግባታቸው ሲረጋገጥ ብቻ በድጋሚ እስከ ሦስት አመት በተጠባባቂነት መድቦ ማሰራት ይቻላል፡፡

(4) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 3 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቢሮው በሦስት ዓመት ውስጥ በተጠባባቂ የተያዙ የትምህርት ቤት አመራር የስራ መደቦች ላይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በምልመላና መረጣ አፈፃጸም መመሪያ መሰረት ውድድር በማካሄድ የትምህርት ቤት አመራሮችን በቋሚነት እንዲመደቡበት ሊያደርግ ይችላል፡፡

(5) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 እና 2 ላይ በተጠቀሰው መልኩ በተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር ስምሪት የተሰጠባቸው የስራ መደቦች በውድድር ቋሚ ምደባ ለትምህርት ቤት አመራሮች እስከሚሰጥ ድረስ የስራ መደቦቹ ክፍት የስራ መደቦች እንደሆኑ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡

(6) በውድድር የትምህርት ቤት አመራር በቋሚነት መመደብ ባልተቻለባቸው የስራ መደቦች ላይ የሚገኙ ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮችን ከ3 ዓመት በላይ ስምሪት በመስጠት ማሰራት አይቻልም፡፡

(7) በትምህርት ቤት በተጠባባቂነት የሚመደብ ርዕሠ-መምህር ከሚያስተምረው ትምህርት ክፍለ ጊዜ ነፃ እንዲሆን እና ተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህሩ እንደ ሚያስተምረው ትምህርት ዓይነት እስከ 10 የትምህርት ክፍለ ጊዜ እንዲያስተምር የሚደረግ ይሆናል፡፡

(8) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተጠቀሰው መልኩ ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህርና ምክትል ርዕሠ-መምህር ከትምህርት ቤቱ መምህራን መካከል መርጦ ለመመደብ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የልዩ ወረዳው ወይም የወረዳው ወይም የከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ከሌሎች አቅራቢያ ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ መምህራን መካከል ፍላጎታቸውንና የውድድር ውጤታቸውን መሰረት በማድረግ በተጠባባቂነት ስምሪት መስጠት ይችላል፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

(9) ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ተደርጎ በተገለጹ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ለትምህርት እርከኑ የተቀመጠውን የትምህርት ዝግጅት የሚያሟሉ መምህራንን በተቀመጡ አማራጮች በመምረጥ ለትምህርት ቤቶች ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህርና ምክትል ርዕሠ-መምህር መመደብ ያልተቻለ እንደሆነ በትምህርት ጽህፈት ቤቱ ማኔጅመንት ሲረጋገጥ የትምህርት እርከኑ ከሚጠይቀው የትምህርት ዝግጅት በአንድ ደረጃ ዝቅ ያሉትን መምህራን ከትምህርት ቤቱ በመምረጥ ስምሪት መስጠት ይቻላል፡፡

(10) በምልመላና መረጣ መመሪያ መሠረት በውድድር ተመርጠው በቋሚነት የተመደቡ ምክትል ርዕሠ-መምህራን በሚገኙባቸው ትምህርት ቤቶች የርዕሠ-መምህር የስራ መደብ ክፍት በሚሆንበት ጊዜ ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር ከምክትል ርዕሠ-መምህራን መካከል በመምረጥ ማሰማራት ይቻላል፡፡ በዚሁ ሁኔታ ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር የሆኑ ምክትል ርዕሠ-መምህራን የተጠባባቂ አበል ሊከፈላቸው የሚችለው በአቻ መምህራን የደረሱበት ደመወዝ ላይ ሲሆን የአቻ መምህራንና የተጠባባቂነት አበል ተደምሮ ለርዕሠ-መምህር ደረጃ ከተፈቀደው መነሻ ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡ የሚበልጥ ከሆነ የተጠባባቂነት አበል ሊከፈል አይችልም፡፡

(11) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 በተጠቀሰው መልኩ የትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕሠ-መምህራን ለትምህርት ቤቱ ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር ለመሆን ፍላጎት ከሌላቸው ከትምህርት ቤቱ መምህራን መካከል በመምረጥ ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር ስምሪት መስጠት ይቻላል፡፡

(12) ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሩ በተጠባባቂነት ተመድቦ የቆየበት ጊዜ ወይም አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ በስራ ልምድነት ይያዛል፡፡

(13) በተጠባባቂ ርዕሠ-መምህርነትና በተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህርነት ተመርጠው የሚሰማሩ መምህራን በተጠባባቂነታቸው ወቅት የቆይታ ጊዜና ሌሎች መስፈርቶችን ካሟሉ እንደ መምህራን በቆይታ ጊዜ ደረጃ ዕድገት በውድድር የሚያገኙ ይሆናል፡፡ ለውድድር ሲቀርቡም የስራ አፈፃጸም ውጤታቸው ከግብ ስምምነት ምዘና ውጤት የሚወሰድ ይሆናል፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

7. <u>የውድድር ማስታወቂያ አወጣጥ</u>

(1) የተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች ስምሪት ለመስጠት ክፍት የትምህርት ቤት አመራር የስራ መደቦች ተጠቅሰው የልዩ ወረዳ ወይም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት በሚገኘው የምልመላ፣ መረጣና ምደባ ኮሚቴ አማካይነት ለ3 ተከታታይ የሥራ ቀናት የውድድር ማስታወቂያ እንዲወጣ በማድረግ የአመልካቾች ምዝገባ ይካሄዳል፡፡

(2) የተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር ወይም የተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህር የውድድር ማስታወቂያ ለትምህርት ቤቱ መምህራን በሙሉ ተደራሽ ሊሆን በሚችል መልኩ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

(3) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 2 ላይ በተጠቀሰው መልኩ ለትምህርት ቤቱ መምህራን የተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር ወይም የተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህር የውድድር ማስታወቂያው ተደራሽ አለመሆኑን የልዩ ወረዳ ወይም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ካመነበት የውድድር ማስታወቂያው ለተጨማሪ ሁለት ቀናት በማራዘም ምዝገባ እንዲካሄድ ማድረግ ይችላል፡፡

(4) የተጠባባቂ ርዕሠ-መምህርና ምክትል ርዕሠ-መምህር የውድድር ማስታወቂያው በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ሁሉ በቀላሉና በግልጽ ሊያዩት በሚችሉበት ሁኔታ በውጪና በውስጥ ማስታወቂያ ሰሌዳ/ ቦታዎች ላይ መለጠፍ አለበት፡፡ የተጠባባቂ ክፍተኛ ሱፐርቫይዘርና የሱፐርቫይዘር የውድድር ማስታወቂያ በትምህርት ጽህፈት ቤት በውስጥ ማስታወቂያ ሰሌዳ የሚለጠፍ ይሆናል፡፡

8. <u>ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር መመልመያ መስፈርት</u>

ትምህርት የሀገሪቱ ልማት ስትራቴጂክ መሳሪያ እንደመሆኑ መጠን ምንጊዜም ቢሆን አስተማማኝና ቁርጠኛ አመራር ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት የተጠባባቂ ትምህርት ቤት አመራር ምልመላ በዘፈቀደ የሚካሄድ ሳይሆን ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በሚከተለው መልኩ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

(1) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህርና ምክትል ርዕሠ-መምህር የመመልመያ መስፈርቶች

ሀ) በትምህርት ቤት አመራር ምልመላና መረጣ መመሪያ ቁጥር 01/2016 እና መመሪያውን ተከትሎ በወጡ ሰርኩላርና ማብራሪያ ላይ በተጠቀሱ የትምህርት መስኮች ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን፤

ለ) በደረጃ ዕድገት መሰላል መለስተኛ መምህር ደረጃና በላይ የደረሱ ወይም 2 ዓመትና በላይ የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህራን፤

ሐ) 2 ዓመትና በላይ የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህራን በማይገኙባቸው ትምህርት ቤቶች ብቻ ከ2 ዓመት በታች ልምድ ያላቸው መምህራን፤

መ) በአባሪ አንድ ላይ በተጠቀሱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ በምልመላና መረጣ መመሪያ ቁጥር 01/2016 እና መመሪያውን ተከትሎ በወጡ ሰርኩላርና ማብራሪያ ላይ በተጠቀሱ የትምህርት መስኮች የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውና በደረጃ ዕድገት መሰላል መለስተኛ መምህር ደረጃና በላይ የደረሱ ወይም 2 ዓመትና በላይ የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህራን፤

ሠ) በዚሁ ንዑስ-አንቀጽ "ሀ" ላይ በተጠቀሰው መልኩ በትምህርት ቤቱ ሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን በማይኖሩበት ጊዜ የልዩ ወረዳው ወይም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት በአቅራቢያ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች በ3 ቀን የጥሪ ማስታወቂያ በመጋበዝ የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ካላቸው አመልካቾች መካከል መርጦ ስምሪት መስጠት ይችላል፡፡

(2) የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህርና ምክትል ርዕሠ-መምህር የመመልመያ መስፈርቶች

ሀ) በትምህርት ቤት አመራር ምልመላና መረጣ መመሪያ ቁጥር 01/2016 እና መመሪያውን ተከትሎ በወጡ ሰርኩላርና ማብራሪያ ላይ በተጠቀሱ የትምህርት መስኮች የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህራን፤

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ Central Ethiopia Regional State Education Bureau

ለ) በደረጃ ዕድገት መሰላል መለስተኛ መምህር ደረጃና በላይ የደረሱ ወይም 2 ዓመትና በላይ የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህራን፣

ሐ) 2 ዓመትና በላይ የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህራን በማይገኙባቸው ትምህርት ቤቶች ብቻ ከ2 ዓመት በታች ልምድ ያላቸው መምህራን ሊወዳደሩ ይችላሉ፤

መ) በአባሪ አንድ ላይ በተጠቀሱ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን ማግኘት በማይቻልባቸው ጊዜ በትምህርት ቤቱ እያስተማሩ በሚገኙበት የትምህርት መስክ በዲፕሎማ የተመረቁ እና በደረጃ ዕድገት መሰላል መለስተኛ መምህር ደረጃና በላይ የደረሱ ወይም 2 ዓመትና በላይ የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህራን ሊወዳደሩ ይችላሉ፤

ሠ) በዚሁ ንዑስ-አንቀጽ "ሀ" ላይ በተጠቀሰው መልኩ በትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን በማይኖሩበት ጊዜ የልዩ ወረዳው ወይም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት በአቅራቢያ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች በ3 ቀን የጥሪ ማስታወቂያ በመጋበዝ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ካላቸው አመልካቾች መካከል መርጦ ስምሪት መስጠት ይቻላል፡፡

(3) ተጠባባቂ ከፍተኛ ሱፐርቫይዘርና ሱፐርቫይዘር የመመልመያ መስፈርቶች

ሀ) በትምህርት ቤት አመራር ምልመላና መረጣ መመሪያ ቁጥር 01/2016 እና መመሪያውን ተከትሎ በወጡ ሰርኩላርና ማብራሪያ ላይ በተጠቀሱ የትምህርት መስኮች ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን፤

ለ) በልዩ ወረዳው ወይም በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ጽህፈት ቤት በዓላማ ፈፃሚ የስራ መደብ ቡድን መሪ ወይም ባለሙያ ወይም በትምህርት ቤት አመራርነት የሰሩባቸው ልምዶች ተደምሮ 6 ዓመትና በላይ የሆኑት፤

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

ሐ) በዚሁ ንዑስ-አንቀጽ “ሀ” እና “ለ” ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸውን ተጠባባቂ ሱፐርቫይዘር ወይም ተጠባባቂ ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር በመምረጥ መመደብ ያልተቻለ እንደሆነ በትምህርት ጽህፈት ቤቱ ማኔጅመንት ሲረጋገጥና በቢሮው ይሁንታ ሲሰጥበት ሱፐርቫይዘር ወይም ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር ከሚጠይቀው የትምህርት ዝግጅት ፀአንድ ደረጃ ዝቅ ያሉትን ባለሙያዎችን/ቡድን መሪዎችን በመምረጥ በውድድር እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡

9. ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር ማወዳደሪያ መስፈርቶች

(1) የምልመላ ሂደቱን አልፈው ለውድድር የቀረቡ ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች በትምህርት ቤት አመራር ምልመላ፣ መረጣና ምደባ አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 01/2016 አንቀጽ 11 በተጠቀሱ ማወዳደሪያ መስፈርቶች እንዲወዳደሩ ተደገርገው በውድድሩ 50ና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች በውጤታቸው ቅደም ተከተል እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡

(2) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የመማር ማስተማሩ ስራ ከተጀመረ በኋላ የሚደረገው የተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች ምልመላና መረጣ በልዩ ወረዳ ወይም በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት አማካይነት ባጠረ ጊዜ ውስጥ እንዲካሄድ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

(3) ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር ምልመላና መረጣ እንዲያካሄድ ውክልና የተሰጠው የልዩ ወረዳ ወይም የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት በትምህርት ቤት አመራር ምልመላ፣ መረጣና ምደባ አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 01/2016 አንቀጽ 11 ከተጠቀሱ የማወዳደሪያ መስፈርቶች መካከል የአመራርነት ብቃት ማወዳደሪያ መስፈርትን ለአንድ ጊዜ ብቻ በመጠቀም ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮችን በማወዳደር መምረጥ የሚቻል ሲሆን በቀጣይ ከቢሮ እውቅና ሲሰጥ በአመራርነት ብቃት ብቻ ማወዳደር የሚቻል ይሆናል፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

(4) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 3 ላይ የተጠቀሰው ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ በትምህርት ቤት አመራር ምልመላ፣ መረጣና ምደባ አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 01/2016 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሠ) ሠንጠረዥ 2 ላይ የተጠቀሱ የአመራርነት ብቃት መመዘኛ መስፈርቶችን ከመምህርነት ለሚመጡት ወይም ከዚህ በፊት የትምህርት ቤት አመራር ላልነበሩት እንዲሁም በሠንጠረዥ 3 ላይ የተጠቀሱ የአመራርነት ብቃት መመዘኛ መስፈርቶችን ከዚህ በፊት የትምህርት ቤት አመራር ለነበሩ እና ከትምህርት ጽህፈት ቤት ለሚቀርቡ ባለሙያዎች ወይም ቡድን መሪዎች በመጠቀም ይሆናል፡፡

(5) ለተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር መረጣ የአመራርነት ብቃት ውጤት የሚሰጠው በልዩ ወረዳ ወይም በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቅራቢነት ውጤቱ በመዋቅሩ ማኔጅመንት በማፀደቅ ይሆናል፡፡ ከ20% የተገኘው የአመራርነት ብቃት በ5 ተባዝቶ ከ100 የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ በውድድሩ 50ና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች በውጤታቸው ቅደም ተከተል እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ፡- ለተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር ያመለከተ መምህር የአመራርነት ብቃት ከ20 የተሰጠው ነጥብ 16 ቢሆን የተሰጠው ውጤት በ5 ተባዝቶ የሚገኘው ነጥብ 80 ይሆናል፡፡

(6) ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች በውድድር ውጤታቸው ተመሳሳይ ሆኖ ለመምረጥ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ በትምህርት ቤት አመራርነት ለተገኘ የስራ ልምድ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ በዚሁም መሰረት መለየት ካልተቻለ በዕጣ እንዲለዩ ይደረጋል፡፡

(7) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ 50ና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች መካከል ሴት አመልካቾች ካሉ ቅድሚያ በመስጠት እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

10. <u>የተጠባባቂነት ወይም የወንበር አበል</u>

(1) ከፍ ያለ ኃላፊነት ወይም የሙያ የስራ መደብ የሚጠይቀውን ተጨማሪ አእምሮአዊና አካላዊ ጥረት ለማካካስ በተጠባባቂነት ለሚመደቡ የትምህርት ቤት አመራሮች የተጠባባቂነት አበል ይከፈላቸዋል፡፡

(2) በተጠባባቂነት የተመደበ የትምህርት ቤት አመራር ከታች በሰንጠረዡ በተመላከተው መነሻ የተፈቀደለትን የተጠባባቂነት ወይም የወንበር አበል በመምህርነት ወይም በጽህፈት ቤት ቡድን መሪነት ወይም ባለሙያነት በሚያገኘው ደመወዝ ላይ ታክሎ ተጨምሮ ይከፈለዋል፡፡

(3) ለተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር የተጠባባቂ አበል የሚሰጣቸው በመምህርነት ወይም በባለሙያነት ወይም በቡድን መሪ ደረጃ በሚከፈላቸው የወር ደመወዝ ላይ ተጨምሮ ይሆናል፡፡ ለተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች የተጠባባቂ አበል ተጨምሮ የሚሰጣቸው በመምህርነት ወይም በባለሙያነት ወይም በቡድን መሪ ደረጃ የሚከፈላቸው ደመወዝ በተጠባባቂነት ለሚመደቡበት የትምህርት ቤት አመራር የስራ መደብ ከተፈቀደው መነሻ ደመወዝ በታች መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

(4) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 3 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር በመምህርነት ወይም በቡድን መሪነት ወይም በባለሙያነት የሚከፈላቸው ደመወዝ ክፍት ለሆነው የትምህርት ቤት አመራር የስራ መደብ ከተፈቀደለት መነሻ ደመወዝ ጋር ተመሳሳይ ወይም ያለፈ ከሆነ የተጠባባቂ አበል አይከፈለውም፡፡ ለምሳሌ፡- ለአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሠ-መምህር የስራ መደብ የተፈቀደው መነሻ ደመወዝ 12,579 ቢሆን በዚሁ ትምህርት ቤት ተጠባባቂ ርዕሰ መምህርነት የሚመረጠው መምህር መነሻ ደመወዙ 12,579 ወይም ከ12,579 በላይ ከሆነ የተጠባባቂነት አበል አይከፈለውም፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

(5) የተጠባባቂነት አበል ተመን:-

| ተ/ቁ | የትምህርት ደረጃ | የስራ መደብ መጠሪያ | የተጠባባቂነት አበል ተመን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሁለተኛ ዲግሪ | ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር | 2,000 | ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ |
| | | ተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህር | 1,850 | |
| | | ተጠባባቂ ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር | 2,000 | በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ በከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት |
| | | ሱፐርቫይዘር | 1,850 | |
| 2 | የመጀመሪያ ዲግሪ | ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር | 1,850 | ለአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እንዲሁም ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
| | | ተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህር | 1,650 | |
| | | ተጠባባቂ ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር | 1,850 | በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ በከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት |
| | | ተጠባባቂ ሱፐርቫይዘር | 1,650 | |
| 3 | ዲፕሎማ | ተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር | 1,650 | ለአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ |
| | | ተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህር | 1,500 | |

(6) የትምህርት ቤት አመራር በውክልና ወይም በተደራቢነት ወይም በጊዜያዊነት ተመድቦ ለሚሰራው ሥራ የተጠባባቂነት አበል አይከፈልም፡፡

(7) በተጠባባቂ ርዕሠ-መምህርነት ወይም በተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህርነት ወይም በተጠባባቂ ሱፐርቫይዘርነት ስምሪት ተሰጥቷቸው የሚመደቡ ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራሮች የተጠባባቂነት አበል የሚከፈላቸው በተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራርነት እስካሉ ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር በዚህ መመሪያ በተገለጹ ጉዳዮች ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ከተጠባባቂ ኃላፊነት የሚለቁ ከሆነ ወይም እንዲለቁና እንዲነሱ ሲደረግ በተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራርነት የሚያገኙት የተጠባባቂ ወይም የወንበር አበል እንዲቋረጥ



በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

ይደረጋል፡፡ ምደባቸውም ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራር ሆነው ከመምጣታቸው በፊት ይሰሩ በነበሩበት ቦታ ወይም የስራ መደብ ላይ ይሆናል፡፡

11. <u>በተጠባባቂነት ለማሠራት ስለሚከለከልበት ሁኔታ</u>

(1) በአባሪ አንድ ከተጠቀሱ ትምህርት ቤቶች በስተቀር ለትምህርት እርከኑ ከሚጠይቀው የትምህርት ዝግጅት በታች ያላቸውን መምህራንን በተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር ወይም በተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህር መርጦ ስምሪት መስጠት አይቻልም፡፡

(2) በቢሮው ይሁንታ ባልተሰጠባቸው የልዩ ወረዳ፣ የወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ክፍት በሆነው የከፍተኛ ሱፐርቫይዘርና የሱፐርቫይዘር የስራ መደብ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን ባለሙያዎች ወይም ቡድን መሪዎች በተጠባባቂ ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር ወይም ተጠባባቂ ሱፐርቫይዘር መርጦ ስምሪት መስጠት አይቻልም፡፡

(3) በክልል ደረጃ በተካሄደው የትምህርት ቤት አመራር ውድድር የተመረጡ የትምህርት ቤት አመራሮች ወይም ተመርጠው በቋሚነት የተመደቡ ወይም ተመርጠው ከተመደቡ በኋላ ምደባ ያቋረጡ ከሆነ በተጠባባቂ ሱፐርቫይዘር ወይም በተጠባባቂ ርዕሠ-መምህር ወይም በተጠባባቂ ምክትል ርዕሠ-መምህር ምልመላና መረጣ ውስጥ ማሳተፍ ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

(4) ተጠባባቂ የትምህርት ቤት አመራርን ከ3 ዓመት በላይ በክፍት የትምህርት ቤት አመራር የስራ መደብ ላይ ማሰራት የተከለከለ ሲሆን እስከዛው ድረስ ክፍት የሆኑ የትምህርት ቤት አመራር የስራ መደቦች ተለይተው በክልል ደረጃ ለሚካሄደው ውድድር ክፍት እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡

(5) ከጽህፈት ቤት ቡድን መሪ ወይም ባለሙያ መካከል ተጠባባቂ ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር ወይም ሱፐርቫይዘር ሆነው በሚመደቡ ጊዜ ቡድን መሪ ወይም ባለሙያ የስራ መደብ ላይ ሌላ ሠራተኛን በቋሚነት መመደብ አይፈቀድም፡፡

(6) በቋሚነት ተመድበው እየሰሩ ከሚገኙ ምክትል ርዕሰ መምህራን መካከል ተጠባባቂ ርዕስ መምህር ሆነው በሚመደቡ ጊዜ በቋሚነት የተመደቡበት የምክትል ርዕሰ መምህር የስራ መደብ ላይ በቋሚነት መመደብ የተከለከለ ነው፡፡

ቋሚ ማኅተም: በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ / Central Ethiopia Regional State Education Bureau

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ የተደነገገውን በቸልተኝነት ያልፈጸመ ወይም ያላስፈጸመ ማንኛውም ኃላፊና ሠራተኛ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

13. ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ጉዳዮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ሌሎች መመሪያዎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ቤት አመራር ምልመላ፣ መረጣ እና ምደባ አፈፃጸም መመሪያ 01/2016 እንዲሁም የትምህርት ቤት አመራሮች የሥራ አፈፃጸም ምዘና መመሪያ ቁጥር 04/2017 የዚህ መመሪያ ደጋፊ ሆነው እስከተገኙ ድረስ በሥራ ላይ ይውላሉ።

14. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች

በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ጥያቄው ለቢሮ እየቀረበ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

15. መመሪያን ስለማሻሻል

ቢሮው እንደአስፈላጊነቱ መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

16. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከህዳር 16 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ወራቤ - ህዳር/2017 ዓ/ም

**አንተነህ ፈቃዱ ወ/ሰንበት**

**የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ምክትል ርዕሰ-መስተዳደር፣**

**የማህበራዊ ክለስተር አስተባባሪ እና ትምህርት ቢሮ ኃላፊ**



በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

| አባሪ/ተቀጽላ 1፡- | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዋናና ምክትል ርዕሰ መምህራን ካልተመደቡባቸው ትምህርት ቤቶች መካከል ለትምህርት እርከኑ የሚጠይቀው የትምህርት ዝግጅት የሚያሟሉ መምህራን የሌሉባቸው ትምህርት ቤቶች | | | | | |
| ተ/ቁ | ዞን/ልዩ ወረዳ | ወረዳ/ ከተማ አስተዳደር | አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች | ወረዳ/ከተማ አስተዳደር | ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
| 1 | ጉራጌ | እንደጋኝ | አጉራ እና አባቴ | ቸሃ | አውያትየ፣ጉ/አውረያ፣የጀከ፣ሞጫ፣ዳቁና፣ቸሀጃቶ እና ጉርዶ |
| | | ገ/ጉ/ወለኔ | ቡርዳ፣ ሁትር፣ የወረች፣ ጎስጣን፣ የበግዬ፣ አንገችማ፣ አምበልታ፣ ዋቦን፣ አመቶ፣ ዃጉድ፣ ጓዝንጓ፣ መጉራጉር፣ አበግራር፣ አዳዘር፣ ባርጣሞ፣ ሀደሮ፣ ቦልጫመኝ፣ ዳረጎት፣ አስፊዲን፣ ቢኔ፣ እሬሶ፣ ቦሮቦር፣ እንደቢዩ ቁ1፣ እንደቢዩ ቁ2፣ ቤደር እና ክሬት | ገ/ጉ/ወለኔ | ደሳ፣ኢንጌ ፣ጉታዘር ፣ጅማ 2ኛ፣ተበተባን እና ወ/ዲሴ |
| | | | | እገሮ | ዋድዬ |
| | | | | አበሽጌ | የረገኤት |
| | | አበሻጌ | ጊቤይባሬ፣አቦ እና ገፈርሳ፣ | እኖር ኤነር | መገርወይራ ፣አንዘቸ እና መገርአንድነት፣ |
| | | ም/አክሊል | ብርሀን፣ጨመኝ፣ድድጋር፣የዘበዥን፣የበጀጨ፣ሴባ፣እነገጀን፣ውርአንፋና እና ዳባ | እኖር | ጋርባዶ፣ሸብራበር፣ጋዛንቾ ፣ጐምሸ፣ ተርሆኝ እና ኢፋንቦሩ |
| | | ጉመር | አበቡጃ፣አሠለጫ፣ካራት በር፣ሱራ፣ጉርማዘር እና በርጨ፣ | ጉመር | እንጃሮ፣ባድ እና ጀንቦሮ |
| 2 | ሀዲያ | ሌሞ | ሰሌጫፌ ፣ እዳይኡላ፣አሼ ኩባኤጋ፣ | | |
| | | አመካ | ጌሜዶ ቁ 2 | | |
| | | ምዕ/ሶሮ | ባዳ ጨከማ | | |
| 3 | ሀላባ | ዌይራ ጂዶ | ጡቃቁ.1፣ቆቦጌቶ፣ኡዳናሚኖ፣ሀንጠዞጋሎ፣በሽኖአድስ፣ወጤጣቁ.1፣ወጤጣቁ.2፣ቁሊቢ፣በንዶቱሎ፣ነጌሌወዴሻ፣ቡቆቲባሜ፣ሀለኬጌሮ፣1ኛ ጡቃ ፣አሎለቃ፣ ቁፌ ቁ.2፣ ሶርጌደርጎሳ፣ መያፋ እና 2ኛ ጡቃ | ዌይራጂዶ | በሽኖ፣ሚቶ፣ሙዳ፣ አቦክቾ እና መቃላ |
| | | አቶቴ ኡሎ | ግርሜ፣ጤሮጨሮ፣ጎፌሳ፣1ኛ ጤሮ፣2ኛ ጤሮ፣ቁንጬዬዬ፣2ኛ ሀንሻ እና ፈልቃ | አቶቴ ኡሎ | ጉባ ፣ሀንሻ እና ጤሮ |
| 4 | ከምባታ | ሀደሮ ዙሪያ | ሀንሠራና እና ቱጻ | | |
| 5 | ምስራቅ ጉራጌ | ሶዶ | ካራ፣አዲስአምባ፣ኤጀርሳ እና ቦኖ አይገዳ | ሶዶ | አዴሎቦርቦር፣ኤጀርሳ፣ዘምዘም እና ዋጮ |
| | | ም/መስቃን | ወጀ ባቲ ቀ.2 እና ዲዳ | ደ/ሶዶ | ዳሙ |
| | | | | ም/መስቃን | ሃሙስ ገበያ እና ዶበና ጎላ |



ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

**አባሪ/ተቀጽላ 1፡-**

**ዋናና ምክትል ርዕሰ መምህራን ካልተመደቡባቸው ትምህርት ቤቶች መካከል ለትምህርት እርከኑ የሚጠይቀው የትምህርት ዝግጅት የሚያሟሉ መምህራን የሌሉባቸው ትምህርት ቤቶች**

| ተ/ቁ | ዞን/ልዩ ወረዳ | ወረዳ/ ከተማ አስተዳደር | አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች | ወረዳ/ከተማ አስተዳደር | ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ስልጤ | አሊቾ | ጨለለቃ፤አጂስገበያ፤ራያ፤ወንተ.ጋ፤ቅጮት፤አንፎ.ታ ፤ኤጎ እና አውሮ | አሊቾ | ጣንዤ፤ጊንዶ፤አብጀት፤ዳ/ዘገር፤ቃዋቆቶ፤ውሪሮ እና አገታ |
| | | ዳሎቻ ወረዳ | መህል ኮሊሳ፤መስዱኔ እና ሄቦትግሪንዝላ | ዳሎቻ ወረዳ | ግሪንዝላ፤ቆሮ ጭሞ እና አንጋሞ ዬዴ |
| | | ሁልባራግ | አባድሮ፤ሞገር፤ጠመዳ፤ዬዴ ሳቦላ፤ቃልቃል እና ህ/የጥቀር | ሁልባራግ | አምበሪቾ |
| | | ላንፉሮ | ጨለለቃ፤ባልጩ ቁ1፤ግራር ቁ2፤ሶስተሮቁ2፤ዶዬ፤ሎላ ቁ2፤ረ/ጩፉና ቁ1፤ፈረጃት፤አምቼ ቁ2፤ገባባ ቁ2 እና ደነብ | ላንፉሮ | ወ/ጎቤ እና ወ/ሎላ |
| | | ምዕራብ አዘርነት | ም/ቀጫ፤አበክሮ፤መንሱር፤ጀኔ፤ገምራ፤አንፋር፤ገበዝ፤ም/ሙጎ፤ቀዴ እና ደማለ አዳኢዶ | ምዕራብ አዘርነት | ኤትሌ፤አንፋር እና ቢላሎ |
| | | ምስራቅ አዘርነት | ቆቶ፤ሞቴ፤የስሬር፤አዋሬ፤ነውርጌ፤አረፎ፤ ሸሻ፤አቁሞ፤ገዋዶ እና ውርበቆቶ | ምስራቅ አዘርነት | አዳዘር |
| | | ሳንኩራ | ቆሬ-ቁ-3፤ ወጤጠ፤ በ/ኩሉፎ፤ ደነብ፤ በ/ሀቁሌ፤ ገ/ዚኮ፤ እ/ጉጣንቾ፤ ረ/ቆሬ፤ ቦኖሻ፤ ፈጠን፤ መ/ሰያቶ፤ ጀ/ሰያቶ፤ ጀ/ለምለም እና በርጮ | ሳንኩራ | ጃታ እና ገተም ጉርባዬ |
| | | ስልጢ | አምብሹሌ፤ኢሎስዶሪ፤ኮምበል፤ሸሌዋሾ እና ዶ/ባቲ | ስልጢ | አዋዬ፤አሳኖ፤ኢሎስ፤አሹቴ እና ኩኖ |
| | | ጦራ | አምቼ እና ግ/ወሬግሴ | | |
| | | ምስራቅ ስልጢ | ሉቄ፤ረጄ፤ዋጮጎቶ፤ቹምቡል እና ሰሜንጎቶ | ም/ስልጢ | ኡዳሳ |
| | | ሚቶ | ሾፎዴ ደባርቅ ቁ.2 | ሚቶ | ኤደነባ |
| 7 | የም | ቶባ | አዛኝ ፤ዱዋ ጎነር፤ ቦታ እና ቶባ | ሶፉ | ሰሙናማ እና ገሲ |
| | | ሶፉ | ሜራ ካሎ ፤ቦኖስር፤አዋሾ እና ሣሣዶ | ቶባ | ቶባ |
| | | ዳርሳጀ ዙሪያ | ጎባ | | |
| | | ፎፋ | ዴሎ | | |
| 8 | ቀቤና | ቀቤና | ቃዋ ቁ1፤ጫንጮ ውጥኝ | ቀቤና | ደቀምሸት ፤ቀቤና 2ኛ እና ወማ |
| 9 | ማረቆ | ማረቆ | ሽርንቶ2ሃፋ ፤ኩኖቀርጠፋ፤ኡዳሳ ረጴ 1ኛ፤ መካከለኛ 1ኛ እና ኢላላ ገቢባ 1ኛ | ማረቆ | ቆሼ 2ኛ ፤ ቢዳራ ፋቃ እና ኡዳሳ ረጴ |
| 10 | ጠምባሮ | ጠምባሮ | | | |